# በ‹‹ወዳጆቹ›› የሚጠቃው የኢትዮጵያ ፕሬስ

*አሜን ተፈሪ*

*08-19-14*

አንዱ መጥቶ፣ ‹‹ሰው ማንን ይመስላል?›› ቢላቸሁ፣ የተለመደወና ቀላሉ መልስ፣ ‹‹ጉሮውን›› የሚል ይመስለኛል፡፡ እንዲህ ያለ መልስ ሊሰጥ የሚችል ሰው፣ ‹‹ፕሬስ ማንን ይመስላል?›› ቢሉት ‹‹በእጅ ሥራ›› ብሂል፣ ተሽቀዳድሞ ‹‹ሐገሬውን›› ወይም ‹‹ሐገሩን›› የሚል ምላሽ ቢሰጥ ተገቢ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ፕሬሶች የረጅም ዘመን ሐገራዊ ታሪክ ‹‹ንዑስ ቅርፀ ምስል›› (Miniturized form) ናቸው፡፡

እኔም እንግዲህ ‹‹ፕሬስ ሐገሬውን ይመስላል›› ብያለሁ፡፡ የሐገሩ መልክ እና ባሕርይም በሐገሩ ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ አምሳል የሚቀረፅ ይመስለኛል፡፡ እንግዲህ ‹‹ብሔራዊ ባህርይ (National character - የሚባል ካለ)፣ የአንድ ሐገር ‹‹መልክ›› እና ባሕርይ በታሪኩ እና በባህሉ የሚታነፅ መሆኑ አይቀርም፡፡

ፕሬስ የባህል እና የታሪክ ነጸብራቅ ነው፡፡ ፕሬሶች፣ ‹‹እኛ ቁባችን ወቅታዊ፣ ዕለታዊና መዋዕለ ዜናዊ ጉዳዮች (current affairs) ናቸው›› ይላሉ፡፡ ትክክል ናቸው፡፡ ግን ደግሞ ‹‹የታሪክን የመጀመሪያ ረቂቅ ንድፍ (The first draft of histroy) የምንፅፍ እኛ ነን›› ይላሉ፡፡ አሁንም ትክክል ናቸው፡፡ ታሪክ፣ ታሪክ የሚሆነው በመጀመሪያ በእነሱ እጅ አልፎ ነው፡፡ እነሱም ዕለታዊ እና መዋዕለ ዜናዊ (current affairs) ጉዳዮችን የሚጽፉት በታሪክ እጅ ተሰርተው ነው፡፡ ለዚህ ነው፣ ‹‹ፕሬሶች የረጅም ዘመን ሐገራዊ ታሪክ ንዑስ ቅርፀ ምስል (Miniturized form) ናቸው›› ያልኩት፡፡

ምሣሌ ፍለጋ፣ እንደ ተለመደው ወደ አውሮፓ እና የአሜሪካ መሄድ አይቀርልንም፡፡ ለምሣሌ፣ የአውሮፓ ፕሬሶች በአይዶሎጂያዊ ጎራ የቆሙ መሆናቸው ይነገራል፡፡ በአሜሪካ ደግሞ እንዲህ ያለ ነገር አይታይም ይላሉ፡፡ የአውሮፓ ፕሬሶች ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር

የተሳሰሩ መሆናቸውን የሚገልጹ ተችዎች፣ የአሜሪካ ፕሬሶች ከዚህ የተለዩ መሆናቸውን ይመሰክራሉ፡፡

ሆኖም፣ ‹‹በአሜሪካ የፓርቲ ልሣን የሚባል ፕሬስ የለም›› ሲባል፣ ለመቀበል መቸገራችን አይቀርም፡፡ ግን የአሜሪካ ፕሬሶችን ከአንዱ የአውሮፓ ሐገር ጋር (ለምሣሌ ከፈረንሳይን) ወስደን፣ በንጽጽር ለማየት ብንሞክር ግልፅ ልዩነት ማስተዋላችን አይቀርም፡፡

ታዲያ ‹‹የአሜሪካ ፕሬሶች አይዶሎጂ እና የፓርቲ ትስስር የላቸውም›› የሚለው ድምዳሜ ሰይፍ የሚያማዝዝ ጭቅጭቅ ሊቀሰቅስ እንደሚችል ባስብም፣ የማርያም መንገድ ለመስጠት ፈቃደኛ ነኝ፡፡ ምናልባት የአሜሪካ ፕሬሶች እንደ አውሮፓዎቹ ግልፅ ወገንተኝነት ለማሳየት ያለመፈለግ ዝንባሌ በማሳየታቸው፣ ይህን ጉዳይ በመለጠጥ የተፈጠረ ድምዳሜ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ሆኖም፣ የአሜሪካ ፕሬሶች ከፖለቲካ ወይም ከአይዲዮሎጂ ነፃ ሆኖ የመታየት ዝንባሌ እንዳላቸው በእርግጠኝነት መመስከር ይቻላል፡፡ አንድ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ፣ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባዊ ድንብን አክብሮ እና ተከትሎ እየሰራ እንደሆነ አስቦ እርካታ ሊያገኝ የሚችለው፣ በተቻለው መጠን ሚዛናዊ እና ገለልተኛ ሆኖ እየሰራ መሆኑን ባሰበ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ምናልባት ገለልተኛ ሆኖ ለመታየት እንደ አሜሪካ ጋዜጦች አይጨነቁ እንደሆነ እንጂ፣ በአውሮፓ ፕሬሶች ውስጥ የሚሰሩ ጋዜጠኞችም ከዚህ የተለየ ስሜት ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ታዲያ ‹‹የአሜሪካ ፕሬሶች አይዶሎጂ እና የፓርቲ ትስስር የላቸውም›› ብለው የሚከራከሩት ወገኖች፣ ‹‹የአሜሪካ ጋዜጦች ከፖለቲካ ገለልተኛ መሆን የቻሉት፣ የፕሬሱ ባለቤቶች በሚከተሉት የጋዜጠኞች ቅጥር መስፈርት ነው›› ይላሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች፣ ‹‹የዲሞክራቶችን የፖለቲካ አቋም የሚደግፍ የፕሬስ ባለቤት፣ በዋና አዘጋጅነት የሚቀጥረው፣ የሪፐብሊካን ፓርቲ አቋም የሚደግፍ ጋዜጠኛን ነው›› ይላሉ፡፡ ይህም ፕሬሶቹ በአይዲዮሎጂ ቅኝት እንይዛነፉ ወይም ሚዛን እንዲጠብቁ አድርጓቸዋል የሚል ሐሳብ አላቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ ራሳቸው ጋዜጠኞቹ፣ ምሁራን፣ ፍ/ቤቶች፣ የፖለቲካ ሰዎች እና መላ ህዝቡ የፕሬስ ነፃነትን የሚጎዳ ችግር ሲመለከቱ፣ ያን ችግር ለማረም የሚያስችል አቋም እና አደረጃጀት ፈጥረው ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ፡፡

‹‹የፕሬሶቹን ባህርያዊ ይዘት የሚወስነው ታሪክ፣ ባህል እና ወግ ነው›› የሚለውን መነሻዬን ለማሳየት ብዙ አልደክምም፡፡ በዚህም ነገር አላራዝምም፡፡ ይህን እንደ ‹‹ፀሐይ በምሥራቅ ትወጣለች›› ያለ እውነት አድርጌ እወስደዋለሁ፡፡ ስለዚህ ታሪክ፣ ባህል እና ወግ፣ በየዘመኑ ነግሶ ከሚወጣ ፖለቲካዊ አጀንዳ ጋር ተዳምሮ፣ በአንድ ታሪካዊ ምዕራፍ የፕሬሱን ቁመና እና መልክ ይቀርፃል፣ ይገልጣል፡፡

ከታሪክ እንደምንመለከተው፣ የአሜሪካ ፕሬሶች ወደ መጀመሪያ አካባቢ፣ እንደኛ ሐገር ፕሬሶች ‹‹ከረር - ቆጣ›› የሚል ድምፀት ገኖ የሚንፀባረቅባቸው ፕሬሶች ነበሩ፡፡ ሆኖም የአሜሪካ ጋዜጠኞች የሙያቸውን ክብር በማስጠበቅ፣ ለስነ ምግባር ደንቦች ተገዢ በመሆን፣ እንዲሁም የፕሬስ ነፃነትን ማስከበር ረገድ፣ ያሳዩት ጀግንነት፣ በጥቅሉ ለሙያቸው ያላቸው ፍቅር እና ትኩረት በህዝቡ ዘንድ ከበሬታን እያተረፈላቸው ሲመጣ፣ በእኛ ዘንድ የሚታየው ተቃራኒ ሁኔታ ነው፡፡ የአሜሪካ ፕሬሶች ህግን በእጅጉ አክብረው የሚሰሩ ናቸው፡፡

በተቃራኒው፣ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች፣ ለሙያቸው እና ለአሰራራቸው መሻሻል የሚበጅ ጥረት ማድረግ አቅቷቸው፣ ሌላው ቀርቶ አንድ የሙያ ማህበር እንኳን ማደራጀት ተስኗቸው፣ እርስ በእርስ በባላንጣ ዓይን እየተያዩ እና እየተጠላለፉ፣ ሙያቸው ጨርሶ በህዝብ ዘንድ ከበሬታን የሚያጣበት ሁኔታ እየተፈጠረ መጥቷል፡፡ የሙያቸውን ክብር ብቻ ሳይሆን፣ ሐገሪቱንም የሚያጠፉ እየሆነ ሄዷል፡፡

ባለፉት የሃያ ዓመታት ጉዞ ለሙያዊ ሥነ ምግባራቸው መከበር የሚሰራ ተቋም ወይም ለይስሙላ እንኳን ስሙ የሚጠቀስ አንድ ድርጅት መፍጠር አልቻሉም፡፡ ከሐገሪቱ ህገ መንግስት መታወጅ ቀድሞ ሥራ በዋለው የ1985 የፕሬስ አዋጅ አማካይነት ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ማጣጣም የጀመሩት የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች፣ ሥራ ላይ ሳለ አንድ ቀን እንኳን ያላመሰግኑትን፣ የ1985 ዓ.ም የፕሬስ አዋጅ፣ እሱን የሚሽር ሌላ አዋጅ በወጣ ጊዜ ያመሰግኑት ጀመሩ፡፡

ዘወትር ችግራቸውን በውጪ አካል ላይ የሚላክኩት የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች፤ ራስን የማየት ትልቅ ጸጋን አጥተዋል፡፡ ራስን የማሻሻል ዕድል አጥተው፤ ከችግራቸው ጋር ቁራኛ ሆኖ ለመኖር ለገድደዋል፡፡ ዛሬም በመዋቅራዊ ችግሮቻቸው ተጠፍረው እንደ ወደቁ ቀርተዋል፡፡ ለዚህ ችግር መቀጠል አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና መኖሩም መዘንጋት የለበትም፡፡

የሐገራችን ፕሬሶች በተሳሳተ ግምት እና እምነት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው፡፡ እንደ መናኛ እና እንደማይረባ ወረቀት የሚያዩትን፤ ሁሌም የሚያጣጥሉትን እና የሚያንቋሽሹትን ህገ መንግስት እንደ ህግ ሰነድ እንኳን የሚቆጥሩት፤ ስለ መብታቸው ሲከራከሩ እና በህግ የሚጠየቁበት ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ ነው፡፡

የህዝቡን አመኔታ እንደ ምስጥ በልተው ጨርሰውታል፡፡ ቀድሞ፤ ‹‹የተጻፈ ነገር ሁሉ እውነት ነው›› የሚል እምነት የያዘ የሚመስለውን የኢትዮጵያ ህዝብ በእነሱ የተበላሸና አልሻሻል ያለ አሰራር የተነሳ፤ ‹‹የተጻፈ ነገር ሁሉ ውሸት ነው›› ወደሚል አመለካከት እየገፉት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት ታሪክ፤ የአጭር ዘመን ታሪክ ነው፡፡ የህገራችን ፕሬሶች፤ በዚህ የአጭር ዘመን የታሪክ ሂደት፤ ለረጅም ዘመን የሚዘልቅ የፕሬስ ደዌ ተክለዋል፡፡ በህዝብ ዘንድ ባለ አመኔታ ረገድ የግል ፕሬሶች ያላቸው ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አንዳንዴ፤ በሚከሰቱ አጋጣሚዎች የአመኔታቸው ደረጃ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለማየት ትችላላችሁ፡፡ በእነሱ ሚዛናዊ ያልሆነ ዘገባ ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች ሳይቀሩ፤ ጉልህ የመጮህ ዝንባሌ ያላቸው አንዳንድ የግል ፕሬሶች የሚያቀርቡት ዘገባ እውነት መሆኑን ይጠራጠራሉ፡፡ ሆኖም፤ የዓላማቸው ደጋፊዎች ሆነው ይጠቅሟቸዋልና እንዲሻሻሉ አይፈልጉም፡፡ ሊወቅሷቸውም አይፈልጉም፡፡ ሆኖም፤ አልፎ አልፎ በከበሬታ ሳይሆን በንቀት እንደሚያይዋቸው ለመረዳት የሚስችሉ አጋጣሚዎች ይከሰታሉ፡፡ በዚህ ረገድ የመንግስት ፕሬሶች የተሸለ ደረጃ ያላቸው ይመስለኛል፡፡

አንዳንዴ፤ በካፌ በረንዳ የተቀመጡ ጓደኛሞች ሲያወሩ፤ አንዱ ‹‹ጋዜጦቹ እኮ እንዲህ አሉ›› ይላል፡፡ ሌላው ‹‹አይ እኔ ይህን አላምንም›› ምላሽ ሲሰጥ፤ ‹‹በኢቴቪም እኮ ቀርቧል፡፡ አዲስ ዘመንም እኮ ዘግቦታል›› ሲሉ ትሰማላችሁ፡፡ ህዝቡ፤ የመንግስት የሚዲያ

ተቋማት ለመንግስት የሚያደላ ዘገባ ይሰራሉ ብሎ ያስባል፡፡ ግን ይዋሻል ብሎ አይገምትም፡፡ እናም ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ ‹‹እንዴ በጋዜጣ እኮ ወጥቷል፡፡ በሬዲዮ እኮ ተነግሯል›› (ሳይንስን በተመለከተ ጉዳይ ሳይቀር) ከሚል የህዝብ አመኔታ፣ ‹‹አይ አንተ የጋዜጦቹን ነገር ይዘህ እንዲህ ትላለለህ›› ወደሚል ደረጃ ወርደናል፡፡

ህዝቡ በገዛ ኑሮው የሚያውቀውን ነገር እየሸፈጡ፣ ነጩን ጥቁር እያደረጉ ሲያቀርቡ አይቷል፡፡ ስለዚህ ይዋሻሉ የሚል አመለካከት አዳብሯል፡፡ ለአንድ የፕሬስ ተቋም ከዚህ በላይ ጉዳት ሊኖር አይችልም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የግል ፕሬሶችን ገዝቶ ሲያነብ ይታያል፡፡ ‹‹ዛሬስ ጋዜጦቹ ምን አሉ›› በሚል፣ ከከተማው ወሬ ተሳታፊ ለመሆን እንጂ፣ በአክብሮት እና በአመኔታ አያነባቸውም፡፡ እናም እንደ ሌላው ሐገር ህዝብ ባለማንበብ አይቀጣቸውም፡፡ አያርቃቸውም፡፡ ይህ ነገር እንደ ባህል ሊቆጠር የሚችል ከሆነ፣ የኢትዮጵያ ፕሬሶች የዚህ ባህል ውጤቶች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል፣ ጉዳዩን ከታሪክ አንጻር ከተመለከትን፣ ከአፄው እና ከደርጉ የአገዛዝ ሥርዓቶች የተወረሱ ባህርያትን በሐገራችን ፕሬሶች ዘንድ መታየታቸው አይቀርም፡፡ በአጭሩ የሐገራችን የፕሬስ ነጻነት ታሪክ ሂደት ሊሻሩ የማይችሉ መጥፎ ውርሶች ይኖራሉ፡፡

የፕሬስ ነፃነት አንድ የህይወታችን የማይነጠል አካል መሆን የጀመረው፣ በዘመነ ኢህአዴግ ነው፡፡ በሐገራችን የፕሬስ ነፃነትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያረጋገጠው አዋጅ ቁጥር 34/85 በሚል የሚታወቀው የፕሬስ ህግ ነው፡፡ ከየሽግግሩ ዘመን መተዳደሪያ ቻርተር የተወለደው የኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት ህግ፣ ታሪክ እና ባህል ተባብረው የሰሩትን የግል ፕሬስ ውጤት ሰጥቶናል፡፡

የሐገራችንን ፕሬሶች ባህርይ ሊደነግጉ የሚችሉ የታሪካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን ብንመረምር፣ ለፕሬስ ነፃነት ዕድገት እና ተግባራዊነት እንቅፋት የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን እንረዳለን፡፡ ሌሎቹን ትተን፣ የቅርብ ጉዳይ ጠቅሰን ነገሩን እንመልከተው፡፡

እንደሚታወቀው፣ የአንድ ስርዓት ሞት እና የሌላ ስርዓት ልደት በሚከናወንበት የታሪክ ምዕራፍ፣ ሁሌም በአሸናፊ እና በተሸናፊ ጎራ የሚሰለፉ ወገኖች ይኖራሉ፡፡ ይህ የታሪክ ምዕራፍ፣ የሽንፈት እና የድል አድራጊነት ስሜት የሚራኮቱበት ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ

ሹመት እና ሽረት በሚስተናገዱበት ወሳኝ ምዕራፍ ወቅት የሚካሄደው ፖለቲካዊ ትግል የእልህ እና ቁጭት ገኖ የሚታዩበት ይናሆል፡፡ እንዲህ ያለ ጊዜ፣ የስሜት ግፊቶች ሰፌ ሚና የሚይዙበት፣ ‹‹አቧራው የሚጨስበት››፣ ሙሾ እና ጎሮ እና ወሸባ ተቀላቅለው የሚሰሙበት፣ አድማጭን የሚያደነቁሩበት ይሆናል፡፡ በዚህ የሽግግር ዘመን ፕሬሱ ያብዳል፡፡ አብዶም ያሳብዳል፡፡ የትናንት ትዝታ እና የነገ ተስፋ የገመድ ጉተታ የሚያደርጉበት ዘመን ይሆናል፡፡ ተስፋ እና ትዝታ ዝብርቅርቅ እንዳሉ ይታጨቃሉ፡፡ በዚህ ወቅት፣ ‹‹ዕብደት›› ፕሬሱ የዘመኑ አሻራ ሆኖ ይወጣል፡፡ በዚህ ተጨባጭ ህይወት አምሳል የተቀረፀ የፕሬስ ‹‹ባህርያዊ›› ጠባይ ይታያል፡፡

ወትሮም ‹‹ወፍ እንዳገሩ ይጮኻልና››፣ ይህን ዘመን ‹‹የዕብደት ዘመን›› ስለሆነ፣ ፕሬሱም ‹‹የዕብደት ጩኸቱን›› አክርሮ እና አግንኖ ያስደምጠናል፡፡ ይህ የዚህች ሐገር ጋዜጠኞች ወይም ልዩ ‹‹መርገምት ወይም ርኩሰት›› አይደለም፣ ሊባል ይችላል፡፡ የአባት ባህርይ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጊዜ ነገሮች ቢከፉ ‹‹ምንም ማድረግ አይቻለም›› ብለን እናልፋቸዋለን፡፡ ዛሬ በሚዛናዊነት እና ገለልተኝነት የሚወደሱት የአሜሪካ ፕሬሶች ‹‹በአንድ ወቅት እንዲህ ያለ የከረረ እና የኮመጠጠ ድምጸት ይታይባቸው ነበር›› መባሉን መፅናኛ አድርገን እንታገሳለን፡፡

ችግሩ፣ ከሃያ ዓመታት በኋላም መፅናኛ የሚሆን ለውጥ አለመታየቱ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ይህ የዕብደት ዘመን ለምን እንዲህ ረዘመ? ስክነት ለመፍጠር መተጋት የነበረባቸው ወገኖች ይህን ኃላፊነታቸውን ለምን አልተወጡም?›› ወዘተ እያልን መነጋገር ይኖርብናል፡፡

አሁንም፣ የፕሬሱ ባህርይ ዋና መገለጫ ዕብደት ለምን ሆነ? ውሎ ሲያድር፣ አደፋፋሪ የዕድገት አዝማሚያ ለምን አላሰየም? ነገ - ከትናንት የተሻለ ይሆናል የሚል ተስፋ ያላሳደረው ለምን ይሆን? የኢትዮጵያ የግል ፕሬስ ነገ የተሸለ መልክ እና ጠባይ ሊይዝ የሚችለው ‹‹ዛሬ እና አሁን›› በሚደረግ ጥረት ነው፡፡ ‹‹ዛሬ እና አሁን›› የሚናየው፣ እንደ ትናንቱ በባላንጣ ዓይን የሚተያዩ ጋዜጠኞችን፣ ለሙያ ሥነ ምግባራቸው መከበር ተደራጅተው መስራት ያቃታቸውን የፕሬስ ሰዎች፣ የህዝቡ መብት እንዲከበር፣ የሐገር ሰላም እንዲጠበቅ፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ዘገባን ለማቅረብ ተግተው የማይሰሩ ጋዜጠኞችን ነው፡፡

በዚህ ዓመት በመንግስት ክስ የቀረበባቸው ጋዜጠኞች የሚሰሩባቸው ፕሬሶች፤ አዘውትረው የሥነ ምግባር እና የህግ ገደብን እየተጋፉ የሚሰሩ ፕሬሶች መሆናቸውን እናያለን፡፡ በእውነት ለመናገር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በመንግስት አሰራር ላይ ትችት በመሰንዘራቸው ጋዜጠኞች ይታሰራሉ የሚለውን ክስ ለመቀበል ይቸግረኛል፡፡ ሆኖም፤ አንዳንድ የውጭ ተቋማት እና ራሳቸው ጋዜጠኞቹ ትችት በመሰንዘራቸው እንደተከሰሱ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ አሁንም እውነት ለመናር፤ ከስድነቱ ወይም ህገ ወጥነቱ ሲቀር፤ ከእነዚህ ክስ ከቀረበባቸው ፕሬሶች በበለጠ፣ የህዝብ አመኔታ ባለው አኳኋን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ዘገባ የሚያቀርቡና የሰላ ትችት የመሰነዝሩ የግል ፕሬሶች አሉ፡፡ በእነዚህ ክስ አልመሠረት አልተመሠረተም፡፡ ስለዚህ ክሱ በህግ የተጠበቁ የግለሰብ፣ የመንግስት፣ የሐገር ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚጥሱ ፕሬሶችን የሚመለከት እንጂ በመንግስት ላይ ትችት የሚሰንዝሩ ፕሬሶችን የሚመለከት አይደለም ለማለት እደፍራለሁ ፡፡

በየሣምንቱ አመፅን የሚቀስቀስ ፅሁፎችን ለዓመታት ሲያትሙ የቆዩ ፕሬሶች መከሰሳቸው ሳይሆን እስከዛሬ ዝም መባላቸው ይበልጥ ይገርመኛል፡፡ ይህን ስርዓት በኃይል ለመጣል በግልፅ የሚሰሩ፣ በሽብርተኝነት የተፈረጁ ኃይሎችን እያሞካሹ እና የጀግና ማዕረግ እያጎናፅፉ ሲያቀርቡ በቆዩ ጋዜጠኞች ክስ ሲመሰረት ማየት ሊገርመኝ አይችልም፡፡

ነፃነትን ሐብቱ ለማድረግ የሚችል ህዝብ፤ ንቁ እናለነፃነቱ ሳይዘነጋ ዘብ መቆም የሚችል ህዝብ ነው፡፡ ሁሌም በውድ መስዋዕትነት የምትገዛውን ‹‹ነፃነት›› የሚሏትን ሰዋዊ ሐብት ከአደጋ መጠበቅ የማይችል ህዝብ፤ ነፃነትን ንብረቱ አድርጓት ሊቆይ አይችልም፡፡

በዲሞክራሲ ገበያ ውስጥ እንደ አሸን በሚርመስመሱ የተለያዩ ፍላጎቶችን ተገን አድርጎ፤ የሚመጣ ነጣቂ አውሬ ውድ ነፃነታችንን እንዳያጠፋ፤ የነፃነትን ግራ አጋቢ መከሰቻዎች በደንብ መርመረን፤ ለአንዱ ህመም መድኃኒት ያለነው መርዝ ሆኖ ነፃነታችንን ለሞት እንዳይዳርጋት ማስተዋል ይኖርብናል፡፡

በርካቶች የኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች እንደ ባህል የያዙት የፍትህ ተቋማትን ማንቋሸሽን፣ በህዝቡ ዘንድ እምነት እንዲያጡ ማድረግን ነው፡፡ እንዲህ የሚያንቋሽሹት ፍ/ቤት በአንዳድ ክሶች በነፃ የሚያሰናብታቸው ተከሳሾች ሲኖሩ፤ የፍ/ቤቱን ውሳኔ የንፅህና

መታወቂያ ካርድ አድርገው ያነሱታል፡፡ ግን ደግሞ ፍርድ ቤቱ ከመንግስት ከተፅኖ ነፃ ያሆነ፤ ፍትሕን ሊሰጥ የማይችል ተቋም አድርገው ያጠለጥሉታል፡፡

አንድ ሰው በመብቱ፣ በነፃነቱ፣ በንብረቱ እና በህይወቱ ላይ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጣበትን ጥቃት የሚከላከልባቸው እንደ ፍርድ ቤት ያሉ የፍትሕ ተቋማት እንዲሻሻሉ እና እንዲጠናከሩ በመስራ ፋንታ፤ ለእነዚህ ተቋማት ጥብቅና በመቆም ፋንታ ዘወትር ሲያራክሷቸው ይታያል፡፡

እንደዚህ ያሉ ተቋማትን ሳይጠብቁ መብቶች እና ነፃነቶች ሊጠበቁ አይችሉም፡፡ በዚህች ሐገር መብቶች እና ነፃነቶች እንዲከበሩ የሚሻ ፕሬስ አመፅ እና ሁከት እንዲነግስ ሳይሆን፤ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን መጣር ይኖርበታል፡፡ የኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት፤ ወዳጆቹ ተብለው በሚታሰቡት ጋዜጠኞች ከፍተኛ ጥቃት የሚፈፀምበት መሆኑን ያለፉት ዓመታት ሁኔታ ያረጋግጥልናል፡፡